የሰ/መ/ቁ. 59294

መጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ.ም.

**ዳኞች** :- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

ዳኜ መላኩ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** :- አቶ በቀለ ጃፋር - ቀረቡ

**ተጠሪ** :- እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ ማሞ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክርክርን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ ሲጀመር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ናቸው፣ ተከሣሽ ደግሞ አመልካች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ ይዘቱ ሲታይ የእናታችንን የውርስ ሀብትና ይዞታ አመልካች ይዞ ስለሚገኝ እንዲለቅልን ይወስንልን የሚል ሲሆን የአሁን አመልካች ለክሱ በሰጡት መከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረቡት የውርስ ሀብት ይገባናል ጥያቄ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የውርስ ሀብቱን ያልያዙ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤትም በአመልካች በቀረበው የይርጋ መቃወሚያ ብይን ሳይሰጥ በማለፉ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅረበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በሁዋላ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት በአመልካች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ሳይሰጥ ማለፉ ሥነ ስርዓቱን የተከተለ አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤት የተፈፀመውን የስነ ስርአት ግድፈት በማረም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ብይን እንዲሰጥ ጉዳዩን መልሶታል፡፡ ከዚህም በሁዋላ የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የአመልካች ማስረጃ እንዲሰሙ ያዘዘ መሆን ያለመሆኑን ማብራሪያ እንዲሰጥና ትእዛዙንም አመልካች አድርሰው ማብራሪያውን እንዲያቀርቡ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ይህንኑ ትዕዛዝ አልፈፀሙም፣ ይልቁንም ቀድሞ ዘርዝረው ያላቀረቡትን የመከላከያ ማስረጃ ዝርዝር አቅርበዋል በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 11 ቀን 2002 ዓ.ም. በፃፉት ሦስት ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ብይን ላይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ አቤቱታቸው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው ነው ተብሎ በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው የፅሑፍ መልሳቸው ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ወሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች ተጠሪዎች ባቀረቡባቸው የውርስ ንብረት ይልቀቅልን የዳኝነት ጥያቄ የይርጋ ክርክር አንስተው የሥር ፍርድ ቤት በዚሁ ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፉ የበላይ ፍርድ ቤት በአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢው ብይን እንዲሰጥ ለስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከመለሰለት በሁዋላ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን ለመስጠት ማስረጃ መስማት እንደአለበት የስር ፍርድ ቤት አምኖ ተገቢ ነው ያለውን ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑ ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ወደዚህ ድምዳሜ የደረሰው ይግባኙን ተመልክቶ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢው መጣራት ተደርጎ ብይን ሊሰጥበት ይገባል በማለት ውሣኔ የሰጠው የበላይ ፍርድ ቤት ተገቢው መጣራት ተደርጓል ሲል ማስረጃ ተሰምቶ መሆን ያለመሆኑን ማብራሪያ እንዲሰጥበት፣ ይህንኑም አመልካች ተከታትለው እንዲያስፈፅሙ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች ይህንኑ ትዕዛዝ ሳያስፈፅሙ አዲስ የማስረጃ ዝርዝር አቅርበዋል በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ያደረገው የጊዜ ማለፍ ሲሆን ይህ የጊዜ ማለፍ ደግሞ ተጠሪዎች ካቀረቡት ክስ ባሕርይ እና ክስ ከተመሰረተበት ጊዜ አንፃር ታይቶ አግባብነት ባለው ሕግ ምላሽ የሚሰጠው ከመሆን ውጪ የተከሣሽ ማስረጃ ሊሰማ የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪዎች የጊዜውን ማለፍ አምነው የይርጋ ጊዜውን ሊያቋርጡ የሚችሉ ሕጋዊ ምክንያት ያላቸው ስለመሆኑ ጠቅሰው ተከራክረው አመልካች ይህንኑ ሊያስተባብል የሚችል ክርክርና ማስረጃ ያላቸው ስለመሆኑ ጠቅሰው መከራከራቸውን የሚያሳይ የክርክር ሂደትም የለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን እንዲሰጥ ይግባኙን የተመለከተው የበላይ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲሰጥም በጊዜው ማለፍ ላይ ማስረጃ እንዲሰማ ብሎ የገለፀው ነገር የሌለ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም በአመልካች በኩል የይርጋ ጊዜ አልፏል በሚል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የክሱን አይነትና ክሱ የቀረበበትን ጊዜ ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማዛመድ ብይን የሚሰጥበት ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት የሰው ማስረጃ መቅረብ አለበት ያለበት አግባብ ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖረው መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ይህ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244/2/ሠ/ እና 234 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎችን ይዘትና መንፈስ እንዲሁም አላማቸውን ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ የአመልካችን የመከራከር መብት ያጣበበ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ከተመለሰለት በሁዋላ መዝገቡን የዘጋበት ሥርዓት መሰረታዊ የሆነ የሥነ ስርዓት ሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለአገኘን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 12832 ጥር 06 ቀን 2002 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00520 መጋቢት 09 ቀን 2002 ዓ.ም.፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 103687 ሐምሌ

03 ቀን 2002 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ የተጠሪዎችን የክስ አይነትና ለጉዳዩ ቀጥተኛ ተፈፃሚነት ያለውን ሕግ መሰረት በማድረግ ተገቢው ብይን ከሚሰጥበት በስተቀር የአመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲሰማ የሚደረግበት ህጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. የሱልልታ ወረዳ ፍርድ ቤት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ጉዳዩን ከዚህ በፊት ባላዩት ዳኛ እንዲታይ በማድረግና በአመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ተገቢውን ብይን በመስጠት ጉዳዩን እንዲዳኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡
4. በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ለአደረጉት ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሽ